የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፩ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.39
ADDIS ABABA 30th March, 2018

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፫/፪ሺ፲ ዓ.ም

የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት (ማሻሻያ) አዋጅ..ገጽ ፲ሺ፫፻፵፫

## Content

Proclamation No.1073/2018

Raw Hides and Skins Marketing (amendment) Proclamation ……………………….Page 10343

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፫/፪ሺ፲

### <u>የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ</u>

የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፬/፪ሺ፭ የግብይት ተዋናዮች ውስጥ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰበሳቢዎችን የማያካትት በመሆኑ በመስኩ ተፈላጊውን ጥራት ማምጣትና ምርትን በአግባቡ መሰብሰብባለመቻሉ አገርንና በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩትን ዜጎች ጭምር ማግኘት የሚገባቸውን ጠቀሜታ ማስጠበቅ እንዲቻል አዋጁን ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፫/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ማሻሻያ</u>**

የጥሬ ቆዳና ሌጦ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፬/፪ሺ፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

### Proclamation No. 1073/2018

### <u>A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF RAW HIDE AND SKIN MARKETING PROCLAMATION</u>

WHEREAS, it has become necessary to amend the existing Raw Hides and Skins Marketing Proclamation No. 814/2013 to include raw hide and skin collectors in the market actors inorder to solve raw hide and skin quality and collecting problems so as to secure economic benefits of the country and people involved in the sector;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Raw Hides and Skins Marketing (amendment) Proclamation No. 1073/2018".

**2. <u>Amendment</u>**

The Proclamation to provide for Raw Hide and Skin Marketing No. 814/2013 is hereby amended as follows:

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፫)፣ (፬)፣ (፰)፣ (፲፰)፣ (፲፱) እና (፳) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፆች (፫)፣ (፬)፣ (፰)፣ (፲፰)፣ (፲፱) እና (፳) ተተክተዋል፤

"፫/ 'ትኩስ ቆዳ ወይም ትኩስ ሌጦ' ማለት እንስሳው ከታረደ ከስድስት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የቀረበ በጨው ያልተዘጋጀ ወይም በአየር ያልደረቀ እርጥብ ቆዳ ወይም ሌጦ ነው፤

፬/ 'ጨው' ማለት የጥሬ ቆዳና ሌጦን ለማዘጋጀት የሚያገለግል እና ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ምግብነት የማይውል ኬሚካል የተጨመረበት ጨው ብሎ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ የሰየመው ነው፤

፰/ 'የግብይት ተሳታፊ' ማለት በጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት የሚሳተፉ አምራቾችን፣ሰብሳቢዎችን፣ አቅራቢዎችን፣ባህላዊ ቆዳና ሌጦ አልፊዎችን፣ የቆዳ ፋብሪካዎችን እና አጓጓዦችን ያካትታል፤

፲፰/ 'የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት' ማለት በጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ለመሰማራት አግባብ ያለው አካል በመመሪያ የሚያወጣውን አስፈላጊውን መስፈርት ላሟላ ሰው የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

፲፱/ 'ሚኒስቴር' ማለት የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር ነው፤

፳/ 'አግባብ ያለው አካል' ማለት እንደ አግባቡ ሚኒስቴሩ ወይም የግብይቱን ሥራ የማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው፤

፪/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፳፫) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፆች (፳፬) ፣(25) ፣(26) እና (27) ተጨምረው ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (፳፬) ንዑስ አንቀጽ (፳፰) ሆኖ ተሸጋሽጓል፤

"፳፬/ "የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢ" ማለት አግባብ ባለው አካል የተመዘገበ ሆኖ ትኩስ ጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት ከሚገኝበት ቦታ ተዘዋውሮ በተመዘገበበት አካባቢ ከግለሰብ አምራች በማሰባሰብ ለጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች ወይም ለባህላዊ ቆዳና ሌጦ አልፊዎች በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ላይ የሚሸጥ ሰው ነው፤

1/ Sub-articles (3) , (4) ,(8), (18),(19) and (20) of Article 2 are deleted and replaced by the following new sub-articles (3), (4) , (8) ,(18),(19) and (20) respectively:

"3/ 'fresh hide or fresh skin' means a fresh hide or fresh skin not treated with salt, not dried by air and supplied within not more than six hours after slaughter of the animal;

4/ 'salt' means a salt designated as chemical salt by the Ethiopian Standards Agency for the treatment of raw hide and skin and not edible by human being and animals;

8/ 'market actor' includes producers, collectors, suppliers, traditional hides and skins processer's, tanneries and transporters participating in hide and skins marketing;

18/ 'certificate of competence' means a certificate issued to a person who fulfills the requirements laid down under a directive issued by the appropriate organ to engage in the marketing of raw hides and skins business ;

19/ 'Ministry' mean Ministry of Livestock and Fishery Resource;

20/ 'appropriate organ' means, as the case may be, the Ministry or a Regional Organ authorized to administer the marketing process;

2/ The following new sub-articles (24), (25), (26) and (27) are added after sub-article (23) of Article 2 of the Proclamation and the existing sub-article (24) is renumbered as sub-article (28) :

"24/'raw hide and skin collector' means a person who, registerd by the appropriate organ and collectes fresh raw hides and skins from producers by travelling in area of his registration and sells to traditional tanners and hides and skins suppliers at first level raw hides and skins market;"

፳፭/ "ክምችት" ማለት በማዘጋጃና በማከማቻ መጋዘን ውስጥ ቁጥሩ እንዲኖር ከሚፈቀደው መጠንና ጊዜ በላይ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ይዞ መገኘት ነው፤

፳፮/ "ደረጃ" ማለት የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ለጥሬ ቆዳና ሌጦ ያወጣው የጥራት ማረጋገጫ ነው፤

፳፯/ "ግለሰብ አምራች" ማለት ለግል ድርጅት የእንስሳት እርድ በመፈፀም ወይም ቤት ለቤት በመዘዋወር የእርድ አገልግሎት በመስጠት ትኩስ ቆዳ ወይም ሌጦን ለሽያጭ የሚያቀርብ ሰው ነው፤"

፫/ ከአዋጁ አንቀጽ ፭ (፪) ፊደል ተራ (ሐ) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ፊደል ተራ (መ) እስከ (ረ) ተጨምረዋል :-

"መ) በግለሰብ አምራቾች እና በጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎች፤

ሠ) በጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎች እና በባህላዊ ቆዳና ሌጦ አልፊዎች፤ እና

ረ) በጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎች እና አቅራቢዎች፤"

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፰) ተሰርዟል፤

፭/ በአዋጁ ከአንቀፅ ፱ (፱) ቀጥሎ የሚከተለው ንዑስ አንቀፅ (፲) ተጨምሯል:-

"፲/ የአካባቢን ብክለት ለመከላከል በወጡ ሌሎች ሕጎች መሠረት ብክለትን በማያስከትል ሁኔታ የመስራት፣የማዘጋጀትና የማስተዳደር፤"

፮/ በአዋጁ ከአንቀፅ ፲፩ (፯) ቀጥሎ የሚከተለው ንዑስ አንቀፅ (፰) ተጨምሯል:-

"፰/የአካባቢን ብክለት ለመከላከል በወጡ ሌሎች ሕጎች መሠረት ብክለትን በማያስከትል ሁኔታ የመስራት፣የማዘጋጀትና የማስተዳደር፤"

፯/ ከአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጾች ፲፪ እና ፲፫ ተጨምረው ነባሮቹ ድንጋጌዎች ከአንቀጽ ፲፪ እስከ አንቀጽ ፲፯ ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፲፬ እስከ ፲፱ ሆነው ተሸጋሽገዋል:-

"**፲፪. <u>የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎች ግዴታ</u>**

ማንኛውም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢ :-

25/ "store" means keeping raw hide and skin over the permitted amount and time in a preparation and storage place

26/ "standard" means raw hide and skin quality assurance set by Ethiopian Standard Agency.

27/ "individual producer" means a person who sell fresh raw hide or skin by giving slaughter service to private organization or door to door slaughter service.

3/ The following new paragraphs (d to f) are added after paragraph (c) of Article 5(2):

"d) individual producers and raw hide and skin collectors;

e) raw hide and skin collectors and traditional raw hide and skin tanners; and

f) raw hide and skin collectors and suppliers;"

4/ Sub-article (8) of Article 5 of the Proclamation is deleted;

5/ The following new sub article 10 is added after Article 9(9) of the Proclamation:

″10/ to work, prepare and administer in a manner not to pollute the environment according to other laws set for environmental protection;

6/ The following new sub article 8 is added after Article 11(7) of the proclamation:

″8/ to work, prepare and administer in a manner not to pollute the environment according to other laws set for environmental protection;

7/ The following new Articles 12 and 13 are added after Article 11 of the Proclamation and the existing provisions from Article 12 to Article 17 are renumbered as Article 14 to Article 19, respectively:

**"12. <u>Obligations of Raw Hides and Hkins Collectors</u>**

Any collector of raw hides and skins shall:

፩/ የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል በወጡ ሌሎች ሕጎች መሠረት ብክለትን በማያስከትል ሁኔታ የመስራት፣ የማዘጋጀትና የማስተዳደር፤

፪/ ትኩስ ቆዳና ሌጦን ከግለሰብ አምራቾች ብቻ የመግዛት፤

፫/ ጥሬ ቆዳና ሌጦን ጥራቱን ጠብቆ የመሰብሰብ፤

፬/ አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ጥሬ ቆዳና ሌጦ እንዲሰበስብ አግባብ ባለው አካል ተመዝግቦ የተሰጠውን ማረጋገጫ የማሳየትም ሆነ የጥሬ ቆዳና ሌጦ የሚያሰባስብበትን ቦታ እንዲጎበኝ የመፍቀድ ግዴታ አለበት

፭/ የአገሪቱን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራትና ግብይት ከሚያጎድፉ ማናቸውም ድርጊቶች የመቆጠብ፤ እና

፮/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያዎችን የማክበር፤

ግዴታዎች አለበት::

**፲፫. የጥሬ ቆዳና ሌጦ ባህላዊ አልፊዎች ግዴታ**

ማንኛውም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ባህላዊ አልፊ :-

፩/ የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል በወጡ ሌሎች ሕጎች መሠረት ብክለትን በመከላከል መስራት፤

፪/ ከሚመለከተው አካል ሥራውን ለመስራት የሚያስችለው የንግድ ፈቃድ የማውጣት፤

፫/ ጥሬ ቆዳና ሌጦን ከአምራች ወይም ከጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎች ብቻ የመግዛት፤

፬/ ጥሬ ቆዳና ሌጦን ያለማከማቸት፤

፭/ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግዥና ሽያጭ መጠን፣ ደረጃና ዋጋ መዝግቦ የመያዝና አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ይህንኑ መረጃ የመስጠት/የማሳየት፤

፮/ አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ማልፊያ ቦታውን እንዲጎበኝ የመፍቀድ፤

1/ work, prepare and administer in a manner not to pollute the environment according to other laws set for environmental protection

2/ buy fresh raw hides and skins only from individual producers;

3/ collect raw hides and skins with maintaining its quality;

4/ Show the appropriate organ, permission letter and allow visit of his raw hides and skins collecting place when requested by the appropriate organ ;

5/ refrain from any activity which may ruin the country's raw hides and skins quality and market; and

6/ respect the provisions of this Proclamation, Regulation and Directives issued hereunder."

**"13. Obligations of Traditional Raw Hide and Skin Tanners**

Any traditional raw hide and skin tanner shall:

1/ work in a manner not to pollute the environment according to other laws set for environmental protection;

2/ have trade license from appropriate organ for his business;

3/ buy raw hides and skins only from producers or from collectors;

4/ not to store raw hides and skins;

5/ record the daily purchase and sales volume of raw hides and skins in quantity, grade and value and give such information to the appropriate organ when requested;

6/ allow the appropriate organ, when requested, to visit his raw hides and skins tanning place;

፯/ የአገሪቱን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራት እና ግብይት ከሚያጎድፉ ማናቸውም ድርጊቶች የመቆጠብ፤ እና

፰/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያዎችን የማክበር፤

ግዴታዎች አሉበት::"

፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፮ (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) እንደተሸጋሸገው) ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፤

"፩/ በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት እንዲገበያይ ካልተፈቀደለት ሰው ጋር የጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦ የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ጥሬ ቆዳ ወይም ሌጦው እንዲወረስ ይደረጋል፤ ሆኖም ለግል ፍጆታው ከሚያመርተው ሰው ውጭ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በተጨማሪ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራትና ከብር ፲፭ሺህ (አስራ አምስት ሺህ) በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::"

## ፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳፩ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ(ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

7/ refrain from any activity which may ruin the country's raw hides and skins quality and market; and

8/ respect the provisions of this Proclamation, Regulation and Directives issued hereunder."

8/ Sub-article (1) of Article 16 (as renumbered pursuant to sub-article (5) of this Article) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ Any person who involves in first level marketing of raw hides or skins with a person not permitted to participate at first level marketing shall be confiscated the raw hides and skins provided, however, that if it is conducted outside the production of house hold consumption, it shall, in addition be punishable with simple imprisonment not exceeding one year and with fine not exceeding Birr 15,000."

## 3. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the *Federal Negarit Gazette.*

**Done at Addis Ababa, this 30th day of March, 2018.**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**